## ጋዜጣዊ መግለጫ

## የኢትዮጵያ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አማራጮች ላይ ሲደረጉ የቆዩ የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች መጠናቀቃቸውን አስመልክቶ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ

የሽግግር ፍትህ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን ከተቋቋመበት ከህዳር 2015 ዓ.ም ጀምሮ የተሰጠውን ኃላፊነት እውን ለማድረግ 'የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አማራጮች በኢትዮጵያ' ሰነድን በማዘጋጀት እና በቀረቡት አማራጮች ላይ የግብአት ማሰባሰቢያ የውይይት መድረኮችን በመምራት ረጅም ርቀት ተጉዞ ዛሬ ያለበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ የሰብአዊ መብት ባለሙያዎች፣ ከጥብቅና ዘርፍ፣ ከሲቪል ማህበረሰብ፣ እና ከፖሊሲ እና ህግ ማርቀቅ ዘርፍ የተውጣጡ 14 ከፍተኛ ባለሙያዎችን በማካተት የተቋቋመው የሽግግር ፍትህ ከፍተኛ የባለሙያዎች ቡድን - ነፃ እና ገለልተኛ የሆነ ጊዜያዊ ቡድን ሲሆን፣ ዋና ተልዕኮውም የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ አማራጮችን ያካተተ የመወያያ ሰነድ ማዘጋጀት፣ በሰነዱ ላይ ሰፊ እና አካታች የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮችን ማደራጀት፣ እና በመጨረሻም የተቀናጀ፣ የተናበበ እና የኢትዮጵያን አውድ ግምት ውስጥ ያስገባ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ማርቀቅ ነው።

ተልእኮውን ከማስፈፀም አንፃርም - የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን - ከዚህ በፊት በርእሰ-ጉዳዩ ላይ ተጀምረው የነበሩ የተለያዩ ስራዎችን፣ ህዳር 2014 ዓ.ም ይፋ የተደረገውን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን እና የተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የጋራ የምርመራ ውጤት ምክረ-ሀሳብን፣ እንዲሁም ጥቅምት 2015 ዓ.ም በተደረሰው የፕሪቶሪያ የሰላም ስምምነት ላይ በመመስረት - ተግባራቶቹን ሲያከናውን ቆይቷል። ቡድኑ ስራውን ሲፈፅም - በክልሎች ከሚገኙ 36 ዩኒቨርሲቲዎች በተውጣጡ 216 የህግ ትምህርት ቤት መምህራን የታገዘ ሲሆን፣ አስተማሪዎቹ በየክልሎቹ በሚካሄዱ የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ላይ የሚሳተፉ ተሳታፊዎችን በመለየት እና በመምረጥ፣ የምክክር መድረኮቹን በማስተባበር፣ እንዲሁም ለተሳታፊዎች የቋንቋ መተርጎም አገልግሎቶችን በመስጠት ከፍተኛ ተሳትፎ እና እገዛ አድርገዋል።

በእስካሁኑ ሂደት የባለሙያዎች ቡድኑ 47 ክልላዊ እና 8 ሀገር-አቀፍ የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮችን አዘጋጅቷል። በተጨማሪም 9 በልዩ ሁኔታ በተለዩ የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ያተኮሩ የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮችን - ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተለያዩ ቢሮዎች፣ ከአፍሪካ ህብረት፣ ከኢጋድ፣ እና ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በቅንጅት አከናውኗል። በነዚህ ውይይቶች ሁሉ የባለሙያዎች ቡድኑ በ12 ክልሎች እና ሁለት የከተማ አስተዳደሮች በመድረስ እና ህዝባዊ ውይይቶችን በማካሄድ - ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን የማወያየት እና ግብአት የመሰብሰብ ስራዎችን ከውኗል። በመሆኑም የመጀመሪያው እና ወሳኝ የሆነውን የግብአት ማሰባሰብ ምእራፍ እያገባደደ ይገኛል።

የምክክሮች ማካሄጃ አጠቃላይ የጊዜ ሰሌዳን በተመለከተ - ቡድኑ የተንዛዛ ሂደትን በማስወገድ - በተቻለ መጠን ሁሉ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን በሰፊው በማሳተፍ በርካታ ግብአትን ለመሰብሰብ በሚያስችል መልኩ ታቅዶ ተግባራዊ ተደርጓል። እንዲያም ሆኖ በቡድኑ ላይ በተፈጠረ ከፍተኛ የስራ ጫና እና ከአቅም በላይ በሆኑ ሁነቶች ምክንያት - ቡድኑ መጀመሪያ ላይ ያወጣውን የአፈፃፀም እቅድ ለመከለስና በተወሰነ ጊዜ ለማራዘም የተገደደ ሲሆን - በፀጥታ ችግር ምክንያትም አምስት የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮችን ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፉ አድርጓል።

ከአካሄድ አንፃር - ሁሉም የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች እና አጠቃላይ የቡድኑ አሰራር ሥርዓት - በሰብአዊ መብቶች መርህ ላይ የተመሰረቱ እና ተጎጂዎችን ማዕከል ባደረገ መልኩ የተከናወኑ ሲሆን፣ በተጨማሪም በአፍሪካ ህብረት የሽግግር ፖሊሲ (2012)፣ በ1996፣ በ2004 እና በ2015 ዓ.ም በወጡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ፀሃፊ ሪፖርቶች፣ እንዲሁም የተባበሩት መንግስታት ከፍተኛ የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ባወጣው የሕግ የበላይነት ሰነድ ላይ በሰፈሩ እሴቶች እና መርሆዎች እንዲመሩ ተደርጓል። የሽግግር ፍትህ ጉዳይ በአገር-መሪነት እና የህዝብ ባለቤትነት ብቻ እንዲመራ የሚያዙት አለም-አቀፍ መርሆችን የመከተል፣ እንዲሁም ስራው ከሁሉም የህብረተሰብ

ክፍሎች ፍላጎት እና ተሰፋ ጋር የተንሰላሰለ እንዲሆን የሚጠይቁ አሰራሮችን የመጠበቅ ግዴታው እንዳለ ሆኖ - ሂደቱ ከበርካታ የባለ-ብዙ እና ሁለትዮሽ ድርጅቶች እና ዓለም-አቀፍ ባለሙያዎች ጋር በከፍተኛ ደረጃ የሚገለፅ ትብብር በመመስረት እንዲመራ ተደርጓል።

የምክክር ሂደቶቹ በኢትዮጵያ ያለውን ልዩ ብዝሀነት ግምት ውስጥ በማስገባት ተከናውነዋል። በግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ላይ ስደተኞች (ኢትዮጵያ ውስጥ የተጠለሉ ስደተኞችን ጨምሮ)፣ የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች፣ አካል ጉዳተኞች እና ህፃናትን የመሳሰሉ የተገለሉ የማህበረሰብ ክፍሎች እንዲሳተፉ በማድረግ - ሂደቱ በአለም-አቀፍ ደረጃ እውቅና የተሰጣቸው የሰብአዊ መብት መርሆችን ባከበረ መልኩ እንዲሳለጥ ተደርጓል። በተጨማሪም የሀይማኖት አባቶች፣ የማህበረሰብ መሪዎች፣ ወጣቶች፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የሚዲያ ባለሙያዎች፣ ምሁራን፣ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች እና አባላት፣ የማህበረሰብ አንቂዎች እና ታዋቂ ሰዎች፣ የንግዱ ማህበረሰብ፣ ሰራተኞች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና በሀገር ውስጥ እና በውጭ ሀገር የሚገኙ የሽግግር ፍትህ ባለሙያዎችን - በተለያዩ ጊዜያት በተዘጋጁ የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች ላይ በሰፊው እንዲሳተፉ አድርጓል። በእያንዳንዱ የግብአት ማሰባሰቢያ መድረክ ላይ 60 በጥንቃቄ የተመረጡ ተሳታፊዎች የተጋበዙ ሲሆን፣ 99% በሚሆኑ መድረኮች ላይ - የተጋበዙት ሁሉም ተሳታፊዎች ተገኝተዋል። ይህም ማህበረሰቡ በዚህ ታሪካዊ ሂደት ላይ ከፍተኛ እምነት ያሳደረ መሆኑን ያሳየ አጋጣሚ ሆኖ አልፏል።

ከከተሞች እና አጎራባች አካባቢዎች የመጡ የተለያዩ የሰብአዊ መብት ጥሰት ሰለባዎች - በግብአት ማሰባሰብ መድረኮቹ ቀዳሚ ትኩረት የተሰጣቸው አካላት ነበሩ። በእያንዳንዱ መድረክ ከተጋበዙ ተሳታፊዎች እስከ 60% የሚደርሱት ሰዎች የሰብአዊ መብት ጥሰት ተጎጂዎች ናቸው። ተጎጂዎች - በልዩ ሁኔታ - በሁሉም መድረኮች በቀረቡ አማራጮች ላይ አቋማቸውን በነፃነት እንዲያንጸባርቁ ወይም የራሳቸውን አማራጮች እንዲያስቀምጡ አስቻይ እድል እንዲፈጠር ተደርጓል። ይህ በተለይ በልዩ መንገድ በተመቻቹ የቡድን ውይይቶች (FGD sessions) የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮች እና ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጋር በመቀናጀት በተዘጋጁ ሁለት "የሴት ተጎጂዎች ብቻ መድረኮች" ላይ ተግባራዊ ተደርጓል። በተጨማሪም ሀገራዊ የግብአት ማሰባሰቢያ መድረኮቹ - ተጎጂዎችን ማእከል ባደረገ አግባብ የሚካሄዱ መሆኑን ለማስረገጥ ሁለት "የሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች ብቻ መድረኮች" እና ሁለት "የስደተኞች ብቻ መድረኮች" ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (ኢትዮጵያ) ጋር በመተባበር ተካሂደዋል።

የምክክር ሂደቱ ፆታዊ እይታን ታሳቢ ያደረገ እና ለፆታዊ ጉዳዮች ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን ለማረገገጥ - ለዚሁ አላማ በተዘጋጀ ፕሮቶኮል እንዲመራ የተደረገ ሲሆን፣ በዚህም በእያንዳንዱ መድረክ ላይ ከተሳተፉ ሰዎች 40% የሚሆኑት ሴቶች እንዲሆኑ ለማድረግ ተችሏል። ሴቶች የሂደቱ ቀዳሚ ባለድርሻ አካል እንደመሆናቸው መጠን በምክክሮቹ ላይ የሚኖራቸውን ተሳትፎ የበለጠ ለማጎልበት እንዲቻል አንድ 'የሴቶች-ብቻ' የሆነ የምክክር መድረክ ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጋር በመተባበር እንዲካሄድ ተደርጓል።

ከተደራሽነት አንፃርም - በሁሉም መድረኮች የተካሄዱ ውይይቶች - በቅድሚያ የሽግግር ፍትህን ፅንሰ-ሀሳባዊ ትንተና እና ትርጉም የሚመለከት ገለፃ በመስጠት እንዲጀመሩ የተደረገ ሲሆን - ይህ አቀራረብ ተጎጂዎች እና አጠቃላይ ተሳታፊዎች የሽግግር ፍትህ ምንነት እና ዓላማን በተመለከተ ግልፅ ግንዛቤ እንዲኖራቸው አስችሏል። ከቋንቋ አጠቃቀም ጋር በተያያዘም - በየክልሎቹ - አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ የትርጉም አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል። ተጎጂዎች እና ሌሎች ተሳታፊዎች የቋንቋዎች አማራጭ የተሰጣቸው ሲሆን - ይህም በትክክል ከመግባባት አንፃር ሊያጋጥሙ የሚችሉ እንቅፋቶችን ለመፍታት እንዲሁም ተሳታፊዎች በውይይቶቹ ላይ ትርጉም ባለው መጠን ሀሳባቸውን እንዲገልፁ እድል ሰጥቷል። በሌላ በኩል - ለግብአት ማሰባሰቢያነት የዋለው የፖሊሲ አማራጮች ሰነድ እና የውይይት መድረኮቹ የሚመሩባቸው ደጋፊ ሰነዶች በኦሮምኛ፣ በትግርኛ እና በሶማሊኛ ቋንቋ አስቀድመው መተርጎማቸው ሂደቱ ውጤታማ እንዲሆን አስተዋፅኦ አድርጓል።

በይዘት ደረጃ - ከተለያዩ አካባቢዎች ወደ ውይይት መድረኮቹ የመጡ ኢትዮጵያውያን - በቀረቡት የሽግግር ፍትህ አማራጮች ላይ ያላቸውን አመለካከት እና የሚመርጡትን ሀሳብ በግልጽ አንፀባርቀዋል። በፖሊሲ አማራጭ ሀሳቦቹ ላይ በነፃነት በመወያየት እና በመከራከር፣ እንዲሁም የነቃ ተሳትፎ በማድረግ - ጠቃሚ የሆኑ ግብአቶችን፣ ትችቶችን እና የራሳቸው ተጨማሪ አማራጮችን ለማቅረብ ችለዋል። በአጠቃላይም ህብረተሰቡ በሂደቱ ሁሉ ያሳየው የነቃ ተሳትፎ እና የባለቤትነት ስሜት እጅጉን ተስፋ የሚያጭር ነበር።

በምክክር ሂደቱ ላይ አሉታዊ አመለካከትን ያንፀባረቁ በጣት የሚቆጠሩ ተሳታፊዎችም ነበሩ። በእርግጥም እንደ ሽግግር ፍትህ ባለ ግዙፍ ሀገራዊ አጀንዳ ላይ የተለያዩ ባለድርሻ አካላት እንደሚኖሩ እና የማይመሳሰሉ አመለካከቶች ሊንፀባረቁ የሚችሉ መሆኑ የሚጠበቅ ጉዳይ ነው። ጥቂት ተሳታፊዎች - በሀገሪቱ አንዳንድ አካባቢዎች የቀጠለው ግጭት እና የፀጥታ ሁኔታ - ለሽግግር ፍትህ ሂደቱ አስቻይ አውድ እንዳይፈጠር እንቅፋት ሊሆን እንደሚችል ስጋታቸውን ገልፀዋል። ሌሎች ውስን ተሳታፊዎች ደግሞ - በሽግግር ፍትህ ፖሊሲው ትግበራ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ተግዳሮቶችን በማንሳት ስጋታቸውን አብራርተዋል። ነገር ግን ሁሉም ተሳታፊዎች - በሽግግር ፍትህ ላይ የተመሰረተ ብሄራዊ መፍትሄ በማፈላለግ አስፈላጊነት ላይ ያላቸውን ፅኑ እምነት ከመግለፃቸውም በላይ፣ የውይይት መድረኮቹን በማደራጀት እና በመምራት ረገድም የባለሙያዎች ቡድኑ ላሳየው ሙያዊ ብቃት አድናቆታቸውን በተመሳሳይ መልክ አንፀባርቀዋል።

በአሁኑ ጊዜ የግብአት ማሰባሰቡ ሂደት የማጠናቀቂያ ምእራፍ ላይ ደርሷል። በእስካሁኑ ጉዞ የባለሙያዎች ቡድኑ ከተሳታፊዎች ከፍተኛ መጠን ያለው ግብአት ያገኘ ሲሆን፣ ከሌሎች ባለድርሻ አካላትም በፅሁፍ የተሰናዱ ምክረ-ሀሳቦችን ተቀብሏል።

የሽግግር ፍትህ አገራዊ ፖሊሲን በማጠናቀቅ ሂደት - በቀጣይ ምእራፍ የሚሰራው ዋና ስራ - የሪፖርት እና የፖሊሲ ረቂቅ ዝግጅትን የሚመለከት ይሆናል። ሪፖርቱ - አጠቃላይ የምክክር ስራዎቹን ሂደት የሚዳስስ፣ እንዲሁም የተሰበሰቡ ግብአቶች አለማቀፋዊ ደረጃን በጠበቀ መንገድ በማጠናቀር እና በመተንተን - ዋና ዋና ግኝቶችን፣ ድምዳሚዎችን እና የሽግግር ፍትህ ዋና ዋና አላባዎችን ማለትም የክስ፣ እውነትን የማፈላለግ፣ የእርቅ፣ የምህረት፣ የማካካሻ፣ የተቋማዊ ማሻሻያ፣ የሽግግር ፍትህ የጊዜ ወሰን፣ እና የባህላዊ አደረጃጀቶች እና የክልሎች ሚና ምንነትን በመዘርዘር - እንዲሁም የቀረቡ ምክረ-ሀሳቦችን በማካተት የሚደራጅ ይሆናል። ቀጥሎም በሪፖርቱ ግኝቶች ላይ የተመሰረተ የሽግግር ፍትህ ፖሊሲ ረቂቅ የሚዘጋጅ ይሆናል። ሪፖርቱም ሆነ ረቂቅ የፖሊሲ ሰነዱ ለህዝብ በይፋ የሚቀርቡ ሲሆን - ፖሊሲው በህዳር 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች በሚደረጉ ተጨማሪ የድህረ-ፖሊሲ ውይይቶች ዳብሮ የመጨረሻ መልኩን የሚይዝ ይሆናል።

የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን - መንግስት በተለይም የፍትህ ሚኒስቴር ለባለሙያዎች ቡድኑ ለሰጠው ሀላፊነት፣ ቡድኑ ተግባራቱን በሙያዊ ነፃነት እና ከጣልቃ-ገብነት ነፃ በሆነ መንገድ እንዲያከናውን ለፈጠረው የፖለቲካ ሁኔታ፤ እንዲሁም ህዝባዊ የውይይት መድረኮቹን በከፊል ፋይናንስ በማድረግ ላደረገው አስተዋፅኦ ምስጋናውን ያቀርባል።

በተጨማሪም የአፍሪካ ህብረት፣ የተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ከፍተኛ ኮሚሽን፣ የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን፣ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሴቶች ፅህፈት ቤት (UNWOMEN)፣ የጀርመን መንግስት ተራድኦ ድርጅት (GIZ)፣ የአሜሪካን ኤምባሲ፣ እና የአሜሪካ አለማቀፍ ልማት ኤጀንሲ (USAID) በሂደቱ ሁሉ ላደረጉት የፋይናንስ እና የቴክኒክ እገዛ የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድኑ ምስጋናውን ይገልፃል።

የሽግግር ፍትህ የባለሙያዎች ቡድን - አዲስ አበባ

ጥቅምት 5 ቀን 2016 ዓ.ም